# የ EI መዝገቦችን ማቆየት እና መጥፋት

የእርስዎ የ EI አገልግሎት አቅራቢ የልጅዎን የ EI መዝገቦች እስከ የልጅዎ ዘጠነኛ ዓመት ልደት ድረስ እንዲይዝ ይጠበቅበታል። ከልጅዎ ዘጠነኛ ዓመት ልደት በኋላ መዝገቦቹ እንዲጠፉ ካልጠየቁ በስተቀር የ EI አገልግሎት አቅራቢው የልጅዎን የ EI መዝገቦችን ከዚህ በላይ ለሆነ ግዜ ይዞ ሊያቆይ ይችላል።

EI የልጅዎን ስም፣ የትውልድ ቀን፣ የመገናኛ መረጃዎን፣ የ EI አገልግሎት አስተባባሪዎች ስም እና ከቤተሰብዎ ጋር የሰሩ አቅራቢዎች እና የመውጫ ዳታን (በመውጫ ጊዜ ያለን አመተ ምህረት እና እድሜን፣ እና ከወጡ በኋላ የገቡባቸው ፕሮግራሞችን ጨምሮ) ያለጊዜ ገደብ ቋሚ መዝገብ አደርጎ ሊይዝ ይችላል።

የልጅዎን የ EI መዝገቦችን በተመለከተ ስለ መብትዎ ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት በ ei@childrenandyouth.ohio.gov ላይ ከ DCY ጋር ይገናኙ።
FERPA ን በተመለከተ ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት በ 202-260-3887 በ የ ዩ.ኤስ የትምህርት ክፍል (U.S. Department of Education) የሚገኘውን የቤተሰብ ተገዢነት ቢሮን (Family Compliance Office) ያነጋግሩ።

# አለመግባባቶችን መፍታት

በ EI ውስጥ ስለ አንድ ነገር አለመግባባት ከተፈጠረ፣ አለመግባባቱን ለመፍታት የሚያስችሉ ብዙ መንገዶች አሉ። በጣም ቀላሉ እና ፈጣኑ መንገድ አለመግባባቱን ለመፍታት ከአካባቢዎ የ EI ፕሮግራም ጋር በእርስዎ የ EI አገልግሎት አስተባባሪ ወይም በካውንቲዎ ውስጥ ባለው የ EI ውል አስተዳዳሪ በኩል መስራት ነው።

የ EI አገልግሎት አስተባባሪዎ አድራሻ መረጃ በዚህ ብሮሹር ላይ ይገኛል። ስለ አካባቢዎ የ EI ፕሮግራም መሪዎች መረጃን የ EI ድህረ-ገጽ በሆነው በዚህ ላይ ያግኙ፡- ohioearlyintervention.org.

በአካባቢዎ የ EI ፕሮግራም በኩል ላለመስራት ከመረጡ፣ የ DCY የ EI ሰራተኞችን በ ei@childrenandyouth.ohio.gov ተጠቅመው ያነጋግሩ።

ለ DODD ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ፣ እና መምሪያው ቅሬታውን እንዲመረምር፣ በሽምግልና ውስጥ እንዲያልፍ ወይም በፍትህ ሂደት ችሎት እንዲታይ መጠየቅ ይችላሉ። ቅሬታዎ ፊርማ ያለው እና በጽሑፍ የቀረበ መሆን አለበት። ምን እንደተከሰተ እና የትኞቹ ደንቦች ወይም መብቶች እንደተጣሱ የሚገልጽ ማብራሪያን ማካተት አለበት።

ቅሬታዎች ወደ ሚከተለው አድራሻ መላክ አለባቸው፡-

Ohio Early Intervention
Ohio Department of Children and Youth
P.O.Box 183204
Columbus, Ohio 43218

# ምርመራ

እርስዎ DCY ቅሬታዎን እንዲመረምር ከፈለጉ መምሪያው ከእርስዎ እና ከ EI አቅራቢዎ መረጃ ይጠይቃል፤ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች ይመረምራል፣ እና በ 60 ቀናት ውስጥ በመብቶችዎ ወይም በ EI ደንቦች ላይ ጥሰት ስለመኖሩ የመጨረሻ የጽሁፍ ውሳኔ ይሰጣል። የመጨረሻው ውሳኔ DCY ማናቸውንም ችግሮች ለማስተካከል ምን እንዳደረገ እና ምን እንደሚያደርግ የተመለከተ ዝርዝር መረጃን ያካትታል።

# ሽምግልና

ሽምግልና በእርስዎ እና በ EI አገልግሎት አቅራቢዎ በኩል በፈቃደኝነት የሚደረግ ነዉ። ሽምግልና ለመጠቀም ከፈለጉ እና የእርስዎ የ EI አገልግሎት አቅራቢ ለመሳተፍ ከተስማማ፣ ሂደቱን ለመቆጣጠር DCY ብቁ እና ገለልተኛ ሽምጋይ ያቀርባል። DCY ለአሸማጋዩ የሚወጣውን ወጪ ይከፍላል፣ እና ሽምግልናው ለተሳታፊዎች በሚመች ቦታ እና ጊዜ መሆን አለበት።

# የፍትህ ሂደት ችሎት

የፍትህ ሂደት ችሎት ይበልጥ መደበኛ የሆነ ሂደት ነው። እርስዎን የሚወክል ጠበቃ መቅጠር ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህ ግዴታ አይደለም። በፍትህ ሂደት ችሎት ላይ ገለልተኛ የፍትህ ሂደት ሰሚ ችሎት መኮንን ቅሬታውን ይመረምራል፣ ተሳታፊዎችን ያዳምጣል፣ ተጨማሪ መረጃን ይገመግማል እና ቅሬታው በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣል። DCY የፍትህ ሂደት ሰሚ መኮንን ወጪን ይከፍላል እና ችሎቱም ለተሳታፊዎቹ አመቺ በሆኑ ቦታዎችና ጊዜያት መሆን አለበት።

ስለ IDEA እና ሰለ Ohio የ EI ፕሮግራም የግዛት ህጎች የበለጠ ለማወቅ፣ohioearlyintervention.org/federal-and-state-regulations ን ይጎብኙ።

**የእኔ የ EI አገልግሎት አስተባባሪ:-**

**የመገናኛ መረጃ፡-**

Department of Children & Youth

Mike DeWine፣ የ Ohio ግዛት ገዥ

Kara B. Wente፣ ዳይሬክተር
Department of Children and Youth
(Rev. 07/2024)

ይህ ተቋም የእኩል ዕድል አቅራቢ እና ቀጣሪ ነው።



# የወላጅ መብቶች

Department of Children & Youth

Help Me Grow Early Intervention

## መግቢያ

በቅድመ ጣልቃ ገብነት (EI) ውስጥ ያሉ ልጆች ወላጆች በአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (IDEA) ስር ብዙ መብቶች እና ጥበቃዎች አሏቸው።

ኦሃዮ የዕደገት አካላዊ ስንክልናዎች ክፍል (Ohio Department of Developmental Disabilities (DODD)) እና የአካባቢ አጋሮቹ በ Ohio ውስጥ የ EI ስርዓትን ያካተቱ ናቸው እና እነዚህን መብቶች እና ጥበቃዎች የመተግበር ኃላፊነት አለባቸው። አብዛኛዎቹ ልጅዎ ለ EI ብቁ ያልሆነ ሆኖ ቢገኝም ይተገበራሉ።

ይህ ብሮሹር ስለ እነዚያ መብቶች እና ጥበቃዎች እንዲሁም በ EI ስላለ አንድ ነገር በተመለከተ አለመግባባት ከተፈጠረ ምን ማድረግ እንዳለቦት ለቤተሰብዎ መረጃ ይሰጣል። በ EI ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቅጾች እነዚህን መብቶች እና ጥበቃዎች ይበልጥ በዝርዝር ያብራራሉ። በተጨማሪም የአገልግሎት አስተባባሪዎም ያብራራቸዋል እና ለሚኖሩዎት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

## የጽሑፍ ቅድመ ማስታወቂያ እና ፍቃድ

በ EI ስርዓት ስለሚሰጡ የተወሰኑ ተግባራት ቀደም ብለው በጽሑፍ መረጃ ያገኛሉ። ይህ “የጽሑፍ ቅድመ ማስታወቂያ” ይባላል። የጽሑፍ ቅድመ ማስታወቂያ በአንድ የተወሰነ ተግባር መቀጠል እንደሚፈልጉ እና እንደማይፈልጉ ለመወሰን ጊዜ ይሰጥዎታል። እንቅስቃሴውን ወዲያውኑ ለመጀመር ዝግጁ ከሆኑ፣ ይህን የጥበቃ ጊዜ አለመጠቀም ይችላሉ። አንዳንድ እንቅስቃሴ ለማድረግ ከወሰኑ በኋላ፣ ፈቃድዎን በጽሑፍ ይሰጣሉ።

ይህ ፈቃድ “ፈቃድ መስጠት” ይባላል። የእርስዎ ስምምነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው እና በማንኛውም ጊዜ ሊሻር ይችላል። ፈቃድዎን ከመስጠትዎ በፊት ስለማንኛውም ተግባር ያልዎት ጥያቄዎችዎ ምላሽ እንደተሰጣቸው የ EI ስርዓቱ ያረጋግጣል። እባክዎን ያሉዎትን ማናቸውንም ጥያቄዎች ለአገልግሎት አስተባባሪዎን ወይም በ EI ውስጥ ከእርስዎ ጋር ለሚሰሩት ያቅርቡ። የጽሑፍ ቅድመ ማስታወቂያ እና የሰጡት ፈቃድ ተግባራዊ የሚሆነው

- ለዕድገት ምርመራዎች፤
- ለልጅ ግምገማዎች፤
- ለልጅ እና ቤተሰብ ግምገማዎች፤
- ለብቁነት ውሳኔ፤ እና
- ግለሰባዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድዎ (IFSP) ላይ አገልግሎቶችን ለመጀመር ወይም ለመቀየር ነው።

በተጨማሪም በእርስዎ IFSP ላይ የተካተተው አገልግሎት ሲያበቃ ወይም ከ EI ሲወጡ የጽሑፍ ቅድመ ማስታወቂያ ይደርስዎታል።

አንዳንድ ሁኔታዎች የጽሑፍ ቅድመ ማስታወቂያን አያካትቱም። የ EI ስርዓቱ የተወሰኑ ድርጊቶችን ከማጠናቀቁ በፊት የእርስዎ ፈቃድ አሁንም ያስፈልጋል።

የ EI ስርዓቱ የሚከተሉትን ነገሮች ከማድረጉ በፊት የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት አለበት፦

- የሕፃናት ሐኪምዎን ጨምሮ ከ EI ስርዓት ውጭ ስለ ቤተሰብዎ መረጃ ከመጋራቱ በፊት፤
- የሽግግር የዕቅድ ጉባኤ ከማካሄድ በፊት፤ ወይም
- ወይም የእርስዎን የህዝብ ወይም የግል ኢንሹራንስ ለ EI አገልግሎቶች ለመክፈል ከመጠቀሙ በፊት።

የልጅዎን ብቁነት ለመወሰን ግምገማ ሊያስፈልግ እንደሚችል እና በ EI ስርዓት እርስዎ አገልግሎት ማግኘት ከመቻልዎ በፊት የልጅ ግምገማ እንደሚያስፈልግ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ለሚካሄድ የልጅ ምዘና ወይም አስፈላጊ ግምገማ ፈቃድዎን ካልሰጡ፣ ልጅዎ በ EI ስርዓት አገልግሎት ማግኘት አይችልም።

## የ EI መዝገቦች እና የእርስዎ ግላዊነት

የ EI ስርዓት ስለ እርስዎ እና ልጅዎ መረጃ የያዘ በመሆኑ፣ በ EI ስርዓት ከተያዙ መዝገቦች ጋር የተያያዙ መብቶች አሉዎት። እነዚህ መዝገቦች እንደ የልጅዎ የEI መዝገብ ይቆጠራሉ እና ስለ ግምገማዎች እና ምዘናዎች መረጃን፣ ከልጅዎ የ EI ብቁነት ጋር የተያያዘ የህክምና መረጃን፣ በእርስዎ IFSP ላይ ያሉ አገልግሎቶችን፣ እርስዎ የሞሉዋቸው እና የፈረሙባቸው የEI ቅጾች ቅጂዎችን ወይም ዋና ቅጂዎችን፣ እና በእርስዎ እና በ EI አቅራቢዎችዎ መካከል ያሉ ግንኙነቶችን የሚያጠቃልሉ ናቸው።

ከቤተሰብዎ የ EI መዝገቦች ጋር የተያያዙ ብዙ መብቶች አሉዎት። እነዚህም የሚከተሉትን የማግኘት መብት ያካትታሉ፦

- የልጅዎን የEI መዝገቦች ቅጂዎች መጠየቅ፤
- ከጠየቁበት አንስቶ በ 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የልጅዎን የEI መዝገቦች የ የመመርመር እና የመገምገም፤
- አንድ ተወካይዎን የልጅዎን የ EI መዝገቦችን እንዲመለከት እና እንዲመረመር ማድረግ፤
- የልጅዎን የ EI መዝገቦች ማብራሪያዎችን እና ትርጓሜዎችን መቀበል፤
- የተሰበሰቡ፣ የተጠበቁ፣ ወይም ጥቅም ላይ የዋሉ የ EI መዝገቦች ዓይነቶች እና ቦታዎች ዝርዝር መኖር፤
- የ EI አገልግሎት አቅራቢው የልጅዎን የ EI መዝገብ እንዲያሻሽል ጥያቄ ማቅረብ፤ እና
- እና አቅራቢው የልጅዎን የ EI መዝገብ ለማሻሻል ፈቃደኛ ካልሆነ የፍትህ ሂደት ችሎት ማግኘት።

ከእንቅስቃሴው በኋላ በ5 ቀናት ውስጥ የብቁነት ውሳኔ ቅጂ (ካለምንም ክፍያ) ይቀበላሉ፣ እና ከእያንዳንዱ የ IFSP ስብሰባ በኋላ በ 10 ቀናት ውስጥ IFSPውን ይቀበላሉ። የ EI መዝገቦችዎን ለማውጣት ክፍያ አይጠየቁም፣ ይሁን እንጂ ክፍያው እነዚያን መዝገቦች የመመርመር እና የመገምገም መብትዎን እስካልከለከለዎት ድረስ አቅራቢዎ ለእርስዎ ለተደረጉት የEI መዛግብት ቅጂዎች ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል።

በእርስዎ የ EI መዝገብ ውስጥ ያለው መረጃ የግላዊነት ባህሪ ስላለው በ EI ስርዓት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች መረጃውን የማግኘት መብት ያላቸው ሰዎች ሚስጥራዊ አድርገው መጠበቅ አለባቸው። ስለ ቤተሰብዎ የ EI መዛግብትን የሚይዙ ኤጀንሲዎች የሚሰበስቧቸውን እና የሚይዟቸውን የ EI መዝገቦች ዓይነቶች እና ቦታዎችን ዝርዝር መያዝ አለባቸው። የእርስዎን የ EI መዝገብ ማግኘት የሚችሉ በ EI ስርዓት ውስጥ ያሉ ሰዎች የእርስዎን ግላዊ መለያ መረጃ (PII) ለሌሎች በ EI ስርዓት ውስጥ ለሚሰሩ ሰዎች ብቻ እና ለቤተሰብዎ የ EI አገልግሎቶችን ለመስጠት በሚያስፈልግበት መጠን ብቻ ማሳወቅ ይችላሉ። የእርስዎ PII ከ EI ስርዓት ውጭ እንዲጋራ ከፈለጉ፣ መጀመሪያ ፈቃደኝነትዎን መስጠት አለብዎት።

ነገር ግን፣ የ 1974 የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) የ EI አገልግሎት አቅራቢዎ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ያለ ወላጅ ፈቃድ PII ን ይፋ እንዲያደርግ ይፈቅዳል። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ለ አካባቢዎ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት እና የግዛት የትምህርት ኤጀንሲ የሚፈለግ የ IDEA ማሳወቂያ ሲሆን። ይህም በእርስዎ የመገናኛ መረጃ እና በልጅዎ ስም እና የተወለደበት ቀን የተወሰነ ነው፤
- የትንበያ ፈተናዎች ለማዘጋጀት፣ ለማረጋገጥ ወይም ለመስጠት፣ የተማሪ እርዳታ ፕሮግራሞች ለማስተዳደር፣ ወይም የትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ዓላማዎች ለትምህርት ኤጀንሲዎች እና ተቋማት ወይም እነሱን ወክለው ጥናቶችን የሚያካሂዱ ድርጅቶች፤
- ማንኛውም ኦዲት፣ ግምገማ፣ ተገዢነት ወይም ከማንኛውም በፌዴራል ወይም በግዛት የተደገፈ የትምህርት መርሃ ግብር ጋር የሚዛመዱ ማንኛውንም የፌዴራል ህጋዊ መስፈርቶችን በተመለከተ የማስፈጸሚያ እንቅስቃሴ ለማካሄድ በዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላይ የሂሳብ ሪፖርት ቁጥጥር (Comptroller General of the United States)፣ በ ዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ በትምህርት ሚኒስቴር ወይም በግዛት ወይም በአካባቢ የትምህርት ባለስልጣን የተሰየመ አካል ወይም ሰው፤
- የኤጀንሲ የጉዳይ ሰራተኛ ወይም ሌላ የግዛት ወይም የአካባቢ የህጻናት ደህንነት ኤጀንሲ ተወካይ ያም ሰው ለልጁ እንክብካቤ እና ጥበቃ በህጋዊ መንገድ ሀላፊነት ያለው ሲሆን፤ እና
- በህጋዊ መንገድ ለተሰጠው የፍርድ ቤት መጥሪያ ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ምላሽ የሚያቀርብ ፍርድቤት።

ከ EI ስርዓት ውጭ የሆነ ሰው የ EI መዝገብዎን ደርሶበት ሲያገኘው፣ መዝገቡን የሚይዘው ኤጀንሲ መዝገቡን ማን፣ መቼ፣ እና ለምን ዓላማ እንደአገኘው የሚገልጽ ሰነድ መያዝ አለበት።